የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
The Ethiopian News Agency

# የአካባቢ ጥበቃ ስራን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፋፋት እንደሚገባ

አዲሰ አበባ, ሰኔ 2 ቀን 2000 (አዲስ አበባ) - የአካባቢ ጥበቃ ስራን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፋት እንደሚገባ የኢፊድሪ ፕሬዚዳንትና የአካባቢ ጥበቃ የበላይ ጠባቂ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ገለጹ፡፡

በአካባቢ ጥበቃና አስተዳደር ላይ የላቀ ስራ እየሰሩ ላሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከፕሬዝዳንቱ እጅ ሽልማት ተሰጥቷልቸዋል፡

ፕሬዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ሽልማቱን በሰጡበት ወቅት እንዳስታወቁት ሕብረተሰቡ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ማሕበረሰባዊ፣ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ ጉዳዩችን ባጣቀሰ መልኩ ትኩረትን እንዲያገኝ በማድረግ ወደ ተግባር የሚገባበትን ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ነው ፡፡

የሽልማቱ ዓላማ በአካባቢ ጥበቃና አስተዳደር ላይ በጎ ስራን እየሰሩ ላሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እውቅና ለመስጠትና እነርሱም ሆነ ሌሎች የተሻለ እንዲሰሩ ለማበረታታት ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ሕብረተሰቡ ለአርአያነት የሚያበቁ በአካባቢ ጥበቃና አስተዳደር ላይ በጎ ምግባራትን የሰሩ አካላትን እውቅና እንዲሰጣቸው እንዲያወድሳቸው ስራዎቻቸውንም በመንከባከብ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት የሚያግዝ በመሆኑ ፕሮግራሙ መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

ይህው ፕሮግራም ቀጣይ ሆኖ ሁሉም ሕብረተሰብ መግስታዊ ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ህግ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች የአካባቢ ችግሮችን በተገቢው መልኩ በማጤን ለመፍትሄው የሚነሳሱበት እንዲሆን ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በመጨረሻም ሶስት ዛፍ ለሶስተኛው ሚሊኒየም መግቢያ ተብሎ የተጀመረው ልማት እንዲፈፀምና ከአምናው የበለጠ እንዲሆን ጥሪያቸውን አስተልፈዋል፡

የአካባቢ ተቆርቋሪዎች መድረክ የቦርድ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር ማስረሻ ፊጠነ በዚሁ ጊዜ እንዳስወቁት ማሕበሩ በተለያዩ አካባቢዎችና ትምህርት ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሕብረተሰቡ በዘርፉ ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

የሽልማት ፕሮግራሙ በመላው አገሪቱ እየተካሔደ ሲሆን የሲቪል ማሕበረሰብ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣የግሉ ክፍሊ ኢኮኖሚንና ወጣቶችን እንዲሁም የላቀ የአካባቢ ጉዳይ ላይ የሚዘግቡ ጋዜጠኞችን ማካተቱን አመልክተዋል

የሽልማት ፕሮግራሙን ያዘጋጀው የአካባቢ ተቆርቋሪ መድረክ አሰተባባሪ አቶ ንጉሱ አክሊሉ በበኩላቸው የአገሪቱን የተፈጥሮ ሃብት በሚገባ ሁኔታ መጠበቁና ጥቅም ላይ መዋሉ ከሰዎች ቁጥጥር ውጪ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ ለመቋቋም የሚኖረውን



**Headlines**

- የአካባቢ ጥበቃ ስራን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፋፋት እንደሚገባ
- በአዲስ አበባ ከተማ በመገንባት ላይ የሚገኙት መንገድና ቤቶች ያጋጠሙ ችግሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የካቢኔ አባላት ጉብኝት አካሄዱ፡፡
- በኢትዮጵያና በጃፖ`ን መካከል የ7 ነጥብ 4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የእርዳታ ስምምነት ዛሬ ተፈረመ፡፡
- በኢትዮጵያ ለአገራዊ ገምገማ የተደረገውን ዝግጅት አስተማማኝነት የሚያረጋግጡ የታዋቂ ሰዎች ፓነል በነገው እለት አዲስ አበባ ይገባል ተብሎ ይጠበቃል፡፡
- በአለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የነዳጅ እና የምግብ ዋጋ ማሸቀብ በአዳጊ አገራት የልማት ጥረት ላይ ትልቅ ፈተና እየደቀነ ነዉ-ሱፊያን አህመድ

አቅም ያሳድጋል ብለዋል፡፡

ሽልማቱ በአመለካከትና በድርጊት ለውጥ በአገሪቱን እውነተኛ የአካብቢ ጥበቃ አብዩት ለማምጣት የሚችል አረንጓዴ ሰራዊት ለመፍጠር እንደሚያስችል አስረድተዋል፡፡

ስ8፡30ሪ1፡00ያ 1፡36

-END---

fe

---END---

(c) The Ethiopian News Agency